# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁጥር 247047

ታህሳስ 30 ቀን 2015 ዓ/ም

**ዳኞች፡-** ብርሃኑ አመነው

በዕውቀት በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ብርሃኑ መንግስቱ

ማርታ ተካ

**አመልካቾች፡-** 1. በሺር ሱሉብ አደን

2. መሀመድ ሱሉብ አደን

**ተጠሪዎች፡-** 1. ሀሰን ራቢ ሀጂ መሀመድ

2. አርዶ ሀጂ መሀመድ

መዝገቡ ሊቀርብ የአመልካች ሰበር አቤቱታ መርምሮ ተገቢውን ትእዛዝ ለመስጠት በሚል ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 12 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሶማሌ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የደገሀቡር ከተማ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 94/2014፤ ሰኔ 14 ቀን 2014ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ማረም ሲገባቸው ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ማጽናታቸው መሠረታዊ የሕግ ስሕተት በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ሊታረም ይገባል በሚል ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ይህ ችሎትም አመልካቾች ያቀረቡትን የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች በየደረጃው ከሰጡት ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሮ ተከታዩን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

## ትዕዛዝ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካቾች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የደገሀቡር ከተማ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ማረም ሲገባቸው ማጽናታቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው በማለት በዋነኝነት አጥብቀው የሚከራከሩበት የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ክስ እንዲያሻሽሉ መፍቀዱና አሻሽለው ያቀረቡት ክስ ላይ አዲስ ፍሬነገር በማካተት ያቀረቡትን የተሻሻለ ክስ ውድቅ ማድረግ ሲገባው መቀበሉ፤ የተጠሪዎችን ክስ በመቃወም የሰጠነው መልስ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥበት ማለፉ፤ተገቢውን ጭብጥ አለመያዙ፤ ተጠሪዎች ምስክሮቻው ሲያሰሙ መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቅ መብታችን መንፈጉ፤ አመልካቾች በኩል የቀረበ ማስረጃ ተገቢውን የማስረጃ ምዘና ሳያደርግና ተገቢውን የክርክር አመራር ስነስርኣት ሳይከተል የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች ማረም ሲገባቸው በማጽናት መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ በዚህ

ሰበር ችሎት ሊታረም ይገባል በሚል ነው፡፡

በስር ፍርድ ቤት የነበረው ክርክር አጠር ባለ መልኩ ይዘቱ ስንመለከት በደገሀቡር ከተማ አስተዳደር ቀበሌ 02 ባአባእዳ ተብሎ በሚጠራው ቦታ በስተጀርባው የሚገኘው ስፍራ የሚገኘው ርዝመቱ 332 ሜትር ስፋቱ 310 የሆነ የእርሻ መሬታችን የአሁኖቹ አመልካቾች በዚህ መሬታችን ላይ መብት ሳይኖራቸው የተወሰነው ቆርጠው በዚህ ሰበር ችሎት ላልተካተቱ ከ3ኛ እስከ 7ኛ ለነበሩት ተከሳሾች በመሸጣቸው እነዚሁ ተከሳሾች የግላቸው ለማድረግ የወሰን ምልክት ያሳረፉበት መሆኑን ጠቅሰው የወሰን ምልክቶች ያደረጉባቸው መሬቶች አሁኖቹ አመልካቾች ጨምሮ ከአመልካቾች የተሸጠላቸው ከ3ኛ እስከ 7ኛ የነበሩት ስር ተከሳሾች በህገወጥ መንገድ የወሰዱትን የእርሻ መሬታቸው እንዲመልሱ እንዲወሰንላቸው ተጠሪዎች አሻሽለው ባቀረቡት ክሳቸው ዳኝነት መጠየቃቸው ያሳያል፡፡

በአሁኖቹ አመልካቾች በኩል ተጠሪዎች ለክሳቸው መነሻ ያደረጉት የወሰን ምልክት የተደረገባቸው መሬት ባለቤቶች አመልካቾቹ እንደሆኑ በስር ፍርድ ቤት ከ3ኛ እስከ 7ኛ ለነበሩት ተከሳሾች የወሰን ምልክት ያደረጉባቸው መሬቶች የሸጡላቸውም አመልካቾች እንደሆኑ ተጠሪዎች በዚህ መሬት ላይ መብት የሌላቸው መሆኑን ገልጸው የተከራከሩ ሲሆን ስር 3ኛ እስከ 7ኛ ያሉት ከአመልካቾች መሬቱ የገዙ መሆኑን ገልጸው ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ በግራቀኙ በኩል ምስክሮች በመስማት እና ወደቦታው በመሄድ በቦታው ከሚገኙ አጎራባቾች የይዞታው አመጣጥ በሚመለከት ማጣራት አድርጎ እንደአጠቃላይ በግራቀኙ በኩል የቀረበ ክርክርና ማስረጃ መሰረት በማድረግ ክርክር ያስነሳው መሬት ባለቤት ሀጂ መሀመድ መሆኑን የእርሻ መሬቱ የገዙት ከ31አመት በፊት ከኡመር ደየል ቤቶች በተለይም ከሀምዲ ኡመር ደየል ከተባለ የገዙ መሆኑን ተጠሪዎች ባቀረቡት ማስረጃ ከአመልካቾች በተሻለ ስላስረዱ ለክሱ መነሻ የሆነው መሬት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተጠሪዎች ነው በማለት ሲወስን፤ የአሁኑ አመልካቾች ስር 3ኛ እስከ 7ኛ ለነበሩት ተከሳሾች የነሱ ያልሆነው መሬት የሸጡላቸው በመሆኑ ካሳ ክፍያ በአሁኑ ወቅት ባለው የመሬት ዋጋ ተገምቶ ሊከፍሉኣቸው ይገባል በሚል ወስኗል ይህንኑ ውሳኔ በየደረጃው ያሉት ፍርድ ቤቶች በመቀበል ያፀኑት መሆኑን ያሳያል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ መንግስት እና ህገ መንግስቱን መሰረት አድርጎ በወጣው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 መሰረት ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመባቸውን ማናቸውንም የመጨረሻ ዉሳኔዎችን መርምሮ ማረምስለመሆኑ የህገ መንግስቱ አንቀጽ 80 (3) (ሀ) እና የአዋጁ አንቀፅ 10 ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ መሠረታዊ የህግ ስህተት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአዋጁ የትርጉም ክፍል በአንቀጽ 2 (4) ስር በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል የሰበር አቤቱታ የቀረበበት የመጨረሻ ዉሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በፌ/ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠ ከሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፤ ሕግን አለግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት ያልሆነ ሕግ የሚጠቅስ፤ ለክርክሩ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤ በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፤ በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፤ ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ፤ የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ፡ ሲሆን ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 2 (4) እና 10 (ሀ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል በማለት የሰበር አቤቱታ ሲቀርብለት ለአቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት ነው ማለት የሚቻለው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ ከላይ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ ቢያንስ አንዱን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 10 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነው፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታውን ተቀብሎ በሰበር የማየት ስልጣን የሚኖረው ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ የሕገመንግስቱን ድንጋጌዎች፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ የሚቃረን ሲሆን እንዲሁም አግባብነት የሌለውን ሕግ በመጥቀስ ወይም ሕግን ያላግባብ በመተርጎም የተሰጠ ውሳኔ/ ትዕዛዝ/ ብይን ሆኖ ጉዳዩም ለሕዝብ ጥቅም አገራዊ ፋይዳ ያለው ጉዳይ የሚመለከት ብቻ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10/1(ሐ)እና(መ) ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ከዚህም

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የምንረዳው የሰበር አቤቱታ የቀረበበት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የተሰጠ ውሳኔ ከእነዚህ ሶስት ሁኔታዎች ውጪ ባሉት ሁኔታዎች መሰረታዊ የሕግ ስሕተት መስፈርት አስመልክቶ በአዋጁ አንቀጽ 2/4 ላይ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን የሚያሟላ ሆኖ ቢገኝ እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጉዳዩን በሰበር የማረም ስልጣን የሌለው መሆኑን ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ/ትዕዛዝ/ብይን በመቃወም የቀረበለት አቤቱታ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለ በኋላ ከሆነ ውሳኔው/ትዕዛዙ/ብይኑ መሠረታዊ የሆነ የሕገ ስሕተት የተፈጸመበት መሆን ያለመሆኑን በመወሰን ረገድ በአዋጁ አንቀጽ 10/1(ሐ)እና(መ) ልዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ የማስገባት ሀላፊነት ይኖርበታል፡፡

በእጃችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስ ለሰበር አቤቱታው ምክንያት የሆነው ጉዳይ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ነው፡፡ አቤቱታው የቀረበውም አዋጅ ቁጥር 1234/2013 ስራ ላይ ከዋለበት ከጥር 13 ቀን 2013 ዓ.ም በኋላ ጥር 12 ቀን 2015 ዓ.ም በመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት የሚኖረው ይኸው አዋጅ ነው፡፡ አመልካቾች ያቀረቡት ሰበር አቤቱታ ከክርክር አመራር ስነስርኣት ጉድለት እና ማስረጃ ምዘና ጉድለት ጋር የተያያዘ ቢሆንም በስር ፍርድ ቤት በግራቀኙ ካከራከረ በኃላ ጭብጥ በመመስረት የግራቀኙ ምስክሮች በመስማትና ለክርክር መነሻ የሆነው ይዞታ አመጣጥ በተገቢው መንገድ በማጣራት ይዞታው የተጠሪዎች መሆኑ ኣረጋግጦ መወሰኑን የሚያሳይ ሲሆን በአመልካቾች በኩል ይዞታው ለስር 3ኛ እስከ 7ኛ ተከሳሾች የሸጥንላቸው እኛ ነን ከማለት ውጭ አመልካቾች ከመነሻውም በይዞታው ላይ መብት ያላቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፤ እንዲሁም መሬት መሸጥ እንደማይቻል በሕግ መንግስቱ አንቀፅ 40 ስር የተደነገገውን በመተላለፍ መሬቱ ለስር 3ኛ እስከ 7ኛ ተከሳሾች መሸጣቸው ህገወጥ ተግባር በመሆኑ በስር ፍርድ ቤቶች ለክሱ መነሻ የሆነው መሬት የተጠሪዎች እንደሆነ በማረጋገጥ የተሰጠው ውሳኔ በአዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4) እና 10/1(ሐ)እና(መ) ላይ ከተቀመጡት መመዘኛዎች አንጻር ሲታይ በዚህ ችሎት ሊታረም የሚችል መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በመሆኑም በፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 28/2 እና ይህንኑ ለማስፈጸም በወጣው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰነ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 17/2015 አንቀጽ 7/1 መሰረት የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ ተደርጓል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የማይነበብ  የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ